ኑር■ አፍሪካ አካዳሚ

አለም አቀፍ በሆነው Y (covid - 19) ኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ት/ቤቶች ላልተወሰነ ግዜያት ዝግ እንድሆኑ መወሰኑ ይታወሳል ። ት/ቤታችንም በተመሳሳይ ችግር ምክንያት ለሁለት ወር ያክል ዝግ ሆኖ ቆይቷል። ችግሩ ከቀን ወደ ቀን ተወግዶ ወደ መደበኛ ስራችን እንመለሳለን ብለን ብናስብም ነገሮች እንዳሰብናቸው ሳይሆኑ ቀርተው እስከ አሁን ቆይተናል። በመሆኑም ይህ ችግር እስከሚያልፍ በማለት የመማር ማስተማሩን ሂደት የምናስቀጥልባቸውን መንገዶች ከወላጅ ኮሚቴዎች ጋር በመነጋገር ውሳኔ አሳልፈን ትምህርቱን በተለያዩ የቪዲዮና ሌሎች መንገዶችን በመጠቀም እየሰጠን መሆኑ ይታወቃል።

ይህንንም የቪዲዮ ት/ት ስንሰጥ ለልጆች የተሻለ የመማር ማስተማር ዘዴ ነው ብሎ በማሰብና የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ለተማሪዎቹ አመርቂና ዘና ብለው እንዲከታተሉ የሚያስችሉ መዝሙሮችን በትምህርቱ ላይ በመጨመር የተዘጋጀ መሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ት/ት መሰረት በማድረግ ተደጋጋሚ ወርክሽቶችና አንዳንድ ፈተናዎች ለተማሪዎች እንዲደርሱ በማድረግና ወላጆችም ይህንን አስከፊ ቀን ከ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚላክላቸውን ወርክ ሽቶችና ፈተናዎች በሚገባ ሁኔታ ሁሉም ወላጆች ባይባልም አሰርተው ልከውልናል።

ት/ቤቱም ይህንን ወርክ ሽትና ፈተና ለተማሪዎች ውጤት እንዲኖረው በማድረግ እየሰራ ይገኛል። አሁንም ይህ አስከፊ ግዜ አልፎ ከምንወዳቸው ብርቅዬ ተማሪዎቻችን ጋር በአካል ተገናኝተን ት/ት እስከሚሰጥ ድረስ ውድ የት/ቤቱ ወላጆች የተለመደውን ትብብር በማድረግ ለልጆች የሚላኩ ቪዲዮዎችን፣ወርክ ሽቶችንና ፈተናዎችን በአግባቡ እንዲከታተሉና የተላከላቸውን የመመዘኛ ጥያቄዎች እያሰሩ በሰዓቱ እንዲመልሱልን ስንገልፅ በታላቅ መተማመን ነው።

በዋነኝነትም የሚላኩ ወርክሽቶችንና ፈተናዎችን በሚሰሩባቸው ግዜ ሊገነዘቧቸው የሚገቡ ነገሮች

1. የተላኩ መፅሀፎች ላይ ከት/ቤቱ በሚሰጥ መመሪያ መሰረት ልጆች በወላጆች እይታ ስር ሆነው በአግባቡ በንፅህና እንዲሰሩ መርዳት
2. የሚሰጡ ወርክ ሽትም ሆነ ፈተናዎችን መሰራት ያለባቸው በተማሪዎቹ ብቻ ሲሆን ወላጆች እንዴት መስራት እንዳለባቸው ብቻ ማብራራት ይችላሉ።
3. ለልጆች ወርክ ሽትም ሆነ ፈተና መስራት በራስ መተማመናቸውን የሚያወርድ ከመሆኑም ባሻገር የልጆቹን ትክክለኛ አቅም ለመለካት የሚያስችል በመሆኑም ተገቢውን ድጋፍና ክትትል እንዳይደረግላቸው ያደርጋል።
4. ወላጆች ለሚኖራቸው ማንኛውም ት/ት ነክ ጥያቄዎች ፣ አስተያየቶች ወይም አሰራሮች ባለፈው በላክንላችሁ የመምህራን ስልክ ቁጥር በመደወል ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ትችላላችሁ።

ተደጋግፈን እንቆማለን

ውድ ወላጅ ይህ ግዜ አልፎ ከልጆቻችን ጋር ዳግም ተገናኝተን ኑር-አፍሪካን እንደምናቆም በፈጣሪያችን ላይ ያለን ተስፋ ላቅ ያለ ነው።

በዚህ ከባድ ወቅት የተማርነው ትልቅ ነገር ቢኖር ኑር-አፍሪካ ያለ ተማሪዎች እንደማይደምቅ የአርስዎ ልጆች ለት/ቤታችን ውበትና ጌጦች መሆናቸው ነው። ምክንያቱም ግቢ ውስጥ ስንገባ የነበረው ያ... የልጅዎ ቡረቃ፣ፈሽታ፣ፈገግታና ፍቅር ዛሬ በሚያስፈራ ጭርታና ፀጥታ ተለውጦ ዛሬ ላይ ስናየው ልባችን በእጅጉ ያዝናል። ነገር ግን ይህ የፈጣሪ ወሳኔ ነውና እንቀበለዋለን። የተሻለ ቀንም ይመጣ ዘንድ ፈጣሪያችንን

እንማፀነዋለን።ኢንሻ አላህ ነገ ብሩህ ቀን እንደሚሆን ተስፋ አለን። ስለዚህ ዛሬ ላይ ተደጋግፈን መቆሙ ግድ ይለናል! በዚህም መሰረት ሁሉም የትምህርት ቤታችን ወላጆች በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ከጎናችን እንድትቆሙ በአክብሮት እንጠይቃለን።

ስለ ኑር-አፍሪካ ይህንን ያውቃሉ?

- ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል አይን በመመልከት አንድን ህፃን ከሌላው ሳያበላልጡ ሲያስተምር መቆየቱን
- በኮሮና ምክንያት ትምህርት እንደተቋረጠ ቀጥታ የኦን ላይን ትምህርት በመጀመር እረገድ የመጀመሪያ መሆኑን
- ለልጅዎ ለውጥ ከልጅ ጀምሮ በፖወር ፖይንት የታገዘ ትምህርት በመስጠት የመጀመሪያ መሆኑን
- ከ ህፃናቱ በተጨማሪ ወላጆችን ለማንቃት የሚደረጉ ስብሰባዎችና የሚሰበሰቡ አስተያየቶች
- ታዲያ ዛሬ ይህ የልጅዎን አይን ማረፊያ የነበረውን ት/ቤትና የልጅዎን ባለ አደራ ወላጅ የነበሩት የት/ቤቱ መምህራን ና ሰራተኞች ህልውና አደጋ ላይ መሆኑንስ ያውቃሉ ?
    - ❖ አንድ እርግጠኛ ሆነን የምንነግራችሁ ነገር ቢኖር ይህ ቀን ከርስዎ ውድ የተማሪዎቻችን ወላጆች ጋር ሆነን እንደምናልፍና ነገ ምንታዘበው ሰው እንዳይኖር ነው።

ት/ቤቱ